# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity



efdpu@aol.com www. Finote.org



**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ነሐሴ 28 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የአመቱ ማጠቃለያ**

**ክፍል አንድ**

****

የወያኔ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ ብቸኛ ሆኖ በሀገሪቱ በስልጣን ላይ ለመቀጠል በነደፈው ስልት መሰረት የካቢኔው ሹም ሽር ላይ ነባሮቹን አግልሎ አዳዲስና ከተማ አመጣሽ ታጋዮችን ሰብስቦ የሾመው በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት መባቻ ላይ ነበር፡፡

በዚሁ አዳማ ላይ ተደረገ በተባለ ለውጥ ነባሮቹን እና ከበረሀ አብረው የመጡትን የብአዴንና የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣኖች በጡረታ እና በአምባሳደርነት ስም ከስልጣናቸው ሙሉ ለሙሉ አባርሮ በምትካቸው አዳዲስ ፍፁም ታማኝና አሽርጋጅ የሆኑትን እንደ እነ ኃይለማርያም ደሳለኝ አይነቶችን ሾሟል፡፡

ኢሕአፓን ክደው ከበረሀ ጀምሮ ለወያኔ ስልጣን መሰረት መጣል ሲተጉ የነበሩትን የብአዴኖቹን ተፈራ ዋልዋና አዲሱ ለገሰን ሙሉ ለሙሉ በጡረታ ሰበብ ያባረራቸው ሲሆን ከህወሀት ደግሞ ስዩም መስፍንን በአምባሳደርነት ሾሞ አሰናብቶዋቸዋል፡፡በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት የሀገሪቱን ስልጣን ከሚስቱ ጋር ጠቅልሎ የያዘው መለስ ዜናዊ ለባለቤቱ አዜብ መስፍን የህወሀት ማዕከላዊ እና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ፤የኢህአዴግ የፖሊት ቢሮ አባልነት፤ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የቁዋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በማድረግ ከመቼውም ግዜ በላይ በስልጣን ላይ ስልጣን ደራርድቦ እጎኑ ሸጉጦ ያስቀመጠታትም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

በለስ የቀናው የከተማ ጮሌው ለመለስ አጎብዳጁ ኃይለማርያም ደሳለኝ ደግሞ ምንም እንኩዋን በተሰጠው ስልጣን ባያዝበትም የአዲሱ ለገሰን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት እና የስዩም

መስፍንን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ስልጣን ደርቦ ሁለቱን ከፍተኛ ስልጣኖች የተሸከመውም በዚሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው::

ለ19 ዓመታት በስልጣን ላይ የቆየው መለስ ዜናዊ እስከ ዛሬ ድረስ ከነበረው የበላይነቱ እጅግ በሰፋ መልኩ ስልጣኑን ከማጠናከሩም በላይ ብቸኛ አምባገነን ሆኖ የወጣበት ዓመት የነበረው የዘንድሮ ነው::

ከአዳማው የካቢኔ ሹም ሽር ከቀናት አስቀድሞ ለስልጣኔ ያሰጉኛል ያላቸውን 10 የህወሀት ነባር ባለስልጣናት በመቀሌ በተደረገ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ከህወሀትም ሆነ ከኢህአዴግ አባልነት የክብር ሰርተፍኬት ተሸላሚ ተብለው ሙሉ ለሙሉ የተባረሩትም በዚሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ ሲሆን ስልጣኑ ሙሉ ለሙሉ በአንድ ግለሰብ እጅ በመውደቁ ሀገሪቱ ውድቀት እንጂ እድገት እንደማታመጣ...... ህዝቡም ለችጋርና ለችግር እንደሚዳረግም በዚሁ ወቅት አንዳንድ ምሁራን ተንብየው እንደነበር አይዘነጋም::

****

በአንድ እራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ ሆኖ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አንዴ በሀገሪቱ ርሀብ አልተከሰተም ሌላ ግዜ ለተራቡት ዜጎች እርዳታ ብንጠይቅም የሚሰማን አጥተናል እያለ እርስ በርሱ የተምታታ መግለጫ የሰጠውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነበር::

የወያኔ ቡድን ሀገሪቱ በሁለት አሀዝ እድገት እያስመዘገበች ትገኛለች እያለ የምዕራባውያኑን ልብ ለማራራት እያለቀሰ ባለበት ወቅት በሀገሪቱ ከ60 ዓመት ወዲህ ባልታየ ሁኔታ ርሀብ ተከስቶ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞት ተዳርገዋል::

የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለተራቡት ዜጎች የአስቸኳዋይ ግዜ እርዳታ እንዲደርስላቸው ጥሪ ሲያቀርብ በአንጻሩ ደግሞ የወያኔ ቡድን ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ጉዳዩን እየሸፋፈነ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ ያንገበገባት እንግሊዝ የርሀብ አደጋ ባጠቃቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ዜጎች አስቸኳዋይ እርዳታ የሚውል 38 ሚሊዮን ፓውንድ በተባበሩት መንግስታት በኩል ለተራቡት ወገኖች እንዲደርስ ያደረገችውም በዚሁ ባገባደድነው ዓመት ነበር::

ምንም እንኩዋን የወያኔ ቡድን በሀገሪቱ ርሀብ እንዳልተከሰተ ቢሸፋፍንም በተፈጠረው ድርቅ ሳቢያ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን እንደ ልጆቻቸው የሚሳሱላቸው 800 ሺህ የቀንድ ከብቶቻቸውም በየቦታው ወድቀው ሽታ በመፍጠሩ ለአካባቢው የአየር መበከል ትልቅ ድርሻ እንደነበረው አይዘነጋም::

በሰሜን ሸዋ፤በአርሲ፤በባሌ፤በምስራቅ ሐረርጌ፤ በምዕራብ ሐረርጌ፤ በቦረና፤በጉጂ ፤በደገሀቡር ፤በቀላፎ ፤በጎዴ፤በጅጅጋ ጭምር የተከሰተውና ስር የሰደደው ርሀብ ከ6 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሞት አፋፍ ላይ ባለበት...... በርሀብ እየተሰቃየ ህፃናት እና አዛውንት አሮጊቶች እየሞቱ የሚቀብራቸው

በጠፋበት ....... የአለም አቀፍ ድርጅቶች ለዜጎቻችን ትኩረት ሰጥተው እየተሩዋሩዋጡ ባለበት ወቅት የወያኔ ቡድን ሰምቶ እንዳልሰማ...... አይቶ እንዳላየ....... አውቆ እንዳላወቀ .......በመምሰል ለጊዜያዊ የፖለቲካው ፍጆታ ሲል ብቻ ርሀብ የለም እያለ ፕሮፓጋንዳ ሲነዛ ነው የከረመው፡፡

ከጥር ወር ጀምሮ የርሀብ አደጋው እንደሚከሰት አስቀድሞ ሲያጠኑና ሲከታተሉ የነበሩ ለጋሽ ድርጅቶች ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጭምር ጥቆማ የሰጡ ቢሆንም ጆሮ ዳባ ልበስ ከማለቱም በተጨማሪ የረድኤት ሰራተኞቹን ያባረረው በዚሁ ዓመት ውስጥ ነው፡፡

እውነት እና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ ሆኖ የወያኔ ቡድን የሁዋላ ሁዋላ ርሀብ መከሰቱን አምኖ ባደረገው የድረሱልኝ ጥሪ መሰረት ለግዜያዊ ፋታ ማግኛ ብቻ የሚሆን 380 ሜትሪክ ቶን የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ገልፆ ይህንንም በገንዘብ ሲያሰላው 329 ዶላር ወይም ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ለግሱኝ ሲል ሲማጸን የተደመጠውም በዚሁ ዓመት ነበር፡፡

በተለይ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ቦረና እና አካባቢው በተከሰተ ርሀብ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ ዜጎች እያለቁ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀባሪ አጥተው እንደሚገኙና ይህን የመሰለ አስከፊ ችግር በዜጎች ላይ እየደረሰ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ ደብቆና ሸፋፍኖ ህዝቡ እንዳያውቅ ቢያደርግም እውነታው ተጋልጦ አደባባይ ሊወጣ ችሎዋል፡፡

****

የወያኔ ቡድን በልማት ስም ህዝብን እያፈናቀለ የከፋ ችግር ውስጥ እየከተታቸው ለርሀብ እና ለእንግልት እየዳረጋቸው ዜጎች ከትውልድ ቀዬአቸው እየተፈናቀሉ የሞቱበት ግዜም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነበር፡፡

ኦሮሚያ፤አማራ፤ጋምቤላ ፤ቤንሻንጉል እንዲሁም አፋር እየተባሉ በሚጠሩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ዜጎች በልማት ስም እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እየተፈናቀሉ ለስደት እና ለሞት ተዳርገዋል፡፡

የአፋር ብሔር ተወላጆችን ከተወለዱበት ቀዬ ለአዋሽ የሸንኮራ ልማት .......ለተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት እና ለውጭ ሀገር ተወላጅ ለሆኑ ኢንቨስተሮች በሚል ብዙ ሺህ ሄክታር መሬት ከነዋሪዎቹና ከተወላጆቹ ላይ ነጥቆ ያባረራቸው ዜጎች ዛሬ ብዙዎቹ በችግርና በችጋር አልቀዋል፡፡

በጋምቤላና በጎንደር ለም መሬቶችን ለቻይና ኢንቨስተሮች በሚል ብዙ ሺህ ሄክታር መሬት ከመስጠቱም በላይ በሀገሪቱ ብቸኛ የደን ቦታ የሆኑትን ሁሉ እየመነጠረ እንዲጨፈጭፉ በመደረጉ ከፍተኛ የደን ሀብት ወድመትም ተከስቶዋል፡፡

በጋምቤላ ለሩዝና ለተለያዩ የእርሻ ልማት ለማዋል በሚል ከሼህ አላሙዲን ጀምሮ ለውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር እያደሉ ህዝቡን እንደባይተዋር እያፈናቀሉ በባለሀብቶቹ የቅኝ ግዛት ስር እንዲወድቁ ተደርጎዋል፡፡

በኦሮሚያ በምዕራብ ሸዋ ዞን በበደኖ ወረዳ አጅላ ዳሌ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ በግብርና ስራ ላይ የሚተዳደሩ 600 አባወራዎች ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት ቀዬ በግዳጅ ከቦታቸው እንዲፈናቀሉ ተደርጎዋል፡፡

ለውጭ ባለሀብቶች ሲባል ከ20 ዓመታት በላይ በቦታው ላይ የኖሩና ቀን ከሌት...... ሀሩር ቁር .......ሳይሉ ሀብትና ንብረት ያፈሩ አልፎ ተርፎ ሚስት አግብተው ልጆች ወልደውና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ከሆኑበት ስፍራ ደፋ ቀና እያሉ ያገኙትን ጥሪት ሁሉ በትነው እንዲወጡና ለስደት እንዲዳረጉ የተደረጉትም ባገባደድነው ዓመት ነው፡፡

ከየክልሉ ለሚነሱና ለሚፈናቀሉ ዜጎች ምትክ መጠለያ ቤት ሳይሰራላቸው....... የካሳ ክፍያ ሳይሰጣቸው ....ለእርሻ የሚሆን ቦታ ሳይዘጋጅላቸው በድንገት ከስፍራው እንዲነሱና እንዲሰደዱ በመደረጉ ዛሬ በየከተማው ተበትነው አስታዋሽ አጥተው ለልመና ተዳርገዋል፡፡

****

ወያኔ በነጋዴው ላይ በቁዋጠረው ቂም የተነሳ በተለያዩ ግዜ የተለያዩ ጫናዎችን እየጫነበት ለማሽመደምድ ብርቱ ጥረት ሲያደርግ የነበረው ከመቼውም ግዜ በላይ በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነው፡፡

ያለ በቂ ጥናት ነጋዴውን እቆጣጠርበታለሁ..... የህዝብ ድጋፍ ደግሞ አገኝበታለሁ ብሎ በግብታዊነት እና በማን አለብኝነት የወሰደው እርምጃ ለከፍተኛ የፖለቲካ ሽንፈት......ኪሳራና ውርደት የዳረገው ከመሆኑም በተጨማሪ ህዝቡም ከምንግዜውም በላይ ለኑሮ ውድነት የተዳረገበት ወቅት ነበር፡፡

የውስጥ ፖለቲካው ተወጥሮ ሊፈነዳ በተቃረበበት እና በኑሮ ውድነት ሳቢያ በሰሜን አፍሪካና በዓረብ ሀገራት የተጀመረው የህዝብ ተቃውሞ እዚህም ይነሳል ብሎ የደነገጠው ወያኔ ነጋዴውን ለማስፈራራት ብሎም የህዝቡን አቅጣጫ ለማስቀየር በሚል ድንገት ሳይታሰብ በተወሰኑ የፍጆታ እቃዎች ላይ የዋጋ ተመን ቢያወጣም መልሶ ሊያነሳ የተገደደውም በዚሁ ዓመት ነው፡፡ በቂ ጥናት ሳይደረግበት...... ሙያተኞች ሳይመክሩበት..... በግብታዊነት የራሱን ችግር ሊቀርፍበት እና ጊዜያዊ ፋታ ለማግኘት ሲል ብቻ በጥቂት የፍጆታ እቃዎች ላይ አውጥቶ የነበረውን የዋጋ ተመን ያነሳ ሲሆን ተመን አወጣሁ ባለ ማግስት ጀምሮ የአንድ ኪሎ ስኩዋር ዋጋ 24 ብር የአንድ ሊትር ዘይት ዋጋ 70 ብር የደረሰውም በዚሁ ወቅት ነበር፡፡

****

ከውስጥ በካድሬዎቹ አተካሮ ሲነሳበት...... ከውጭ በሰብአዊ መብት ረጋጭነቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጫናዎች ሲደርሱበት...... እና የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው መለስ ዜናዊ ለጊዜያዊ ፋታ ማግኛ ይሆነኛል በሚል እጃቸው በሰው ልጆች ደም የጨቀየውን እና በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከስሰው የሞት ፍርድ የተወሰነባቸው የደርግ ባለስልጣናትን በብሔራዊ እርቅ ስም ከእስር ለማስፈታት ደፋ ቀና ሲል ቢከርምም የሙዋች ቤተሰቦች እና የሰማዕታት አሰባሳቢ ኮሚቴ አመራሮች በመቃወማቸው ጉዳዩ ሳልተወሰነ ግዜ ሊተላለፍ የቻለው በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነበር።

የደርግ ባለስልጣናትን በብሔራዊ እርቅ ሽፋን ከእስር የማስፈታቱ ሂደት በእምነት አባት ነን በሚሉት በእነ አባ ገብረመድህን በኩል ጥረት ሲደረግ የነበረ ቢሆንም በህዝቡ እና በሰማዕታት ቤተሰቦች ቆራጥ ተቃውሞ መለስ ያሰበው ሳይካለት ደርጎችም ሳይፈቱ ዓመቱ ተጠናቅቆዋል።

የሀገሪቱ የቁርጥ ቀን በሆኑት በኢህአፓ ወጣቶች፤ ምሁራን፤ ታጋዮች እና በመላ ሀገሪቱ ህዝቦች ላይ አሰቃቂ ግፍ እና ስቃይ ለ17 ዓመታት ሲያደርሱ የነበሩት የደርግ ባለስልጣናት በወንጀለኛ ው ወያኔ ቡድን የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ግዜያቸውን ሲጠባበቁ ባለበት ወቅት በብሔራዊ እርቅ ሰበብ መፈታታቸው እንደማይሆን ያረጋገጠው ወያኔ በፐሬዝዳንቱ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በኩል የሞት ፍርዱ ወደ እድሜ ልክ እንዲቀየርላቸው ያደረገውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነበር።

የሀገሪቱ ህዝቦች በወያኔ አልሞ ተኩዋሽ ቅልብ ወታደሮች እየተዘነጠሉ በየአደባባዩ ሲገደሉ ትንፍሽ ያላሉት የእምነት አባት ነን ባዮቹ እነ አባ ገብረመድህን መለስ ዜናዊ የውስጥና የውጭ የፖለቲካ ኪሳራ ሲደርስበት ለመጠገን ሲሉ በብሔራዊ እርቅ ሰበብ የደርግ ባለስልጣናትን ለማስፈታት ከላይ ታች ሲሉ ቢከርሙም ያሰቡት ሳይሳካ ያለሙት ሳይሆን ዓመቱ ተገባድዶዋል።

ዜጎች በወያኔ የግፍ ሰለባ ሆነው በየእስር ቤቱ እየማቀቁ እና እየተንገላቱ ጠያቂ አጥተው ከዘመድ አዝማዶቻቸው እንዳይገናኙ ተከልክለው በጠባብ ክፍል ታጉረው አስታዋሽ አጥተው ባሉበት በዚህ ግዜ የወያኔው ፖለቲካ አራማጅ የሆኑት የእምነት አባት ነን ባዮቹ እነ አባ ገብረመድህን ለደርግ ባለስልጣናት እና የወያኔን ፖለቲካ ለመጠገን ሲሉ ጠብ እርግፍ እያሉ ባለበት ወቅት የመንግስቱ ኃይለማርያም ቀኝ እጅ እና ምስጢር ጠባቂ የነበረው የደህንነት ሚኒስትሩ ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴ በደስታ ይሁን በድንጋጤ....... በህመም ይሁን በድብደባ......የደርግ ባለስልጣናት ሊፈቱ ነው ተብሎ ውዥንብር እየተነዛ በነበረበት ሰሞን በድንገት ሞተ የተባለውም በዚው ሰሞን ነበር።

****

በወያኔ የአገዛዝ ዘመን ለመጀመሪያ ግዜ የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆኑት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን ለሶስት ቀናት የስራ ጉብኝት ለማድረግ ይመጣሉ ተብሎ ሽብ ረብ ሲሉ የከረሙብትና ለግማሽ ቀን ብቻ ውሎ ገባ ደርሰው የተመለሱበት ዓመትም ይሄው ያሳለፍነው ዘመን ነበር።

የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ እና አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች ከቻይና ጋር እየተሞዳሞዱ ባ ሉበት ወቅት የአሜሪከ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በአፍሪካ ህብረት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተገኝተው

የአፍሪካ ተወካዮች በተገኙበት ለረዥም ሰዓት በቆየው ማስጠንቀቂያ አዘል ንግግራቸው አፍሪካ ውስጥ የውጭ ባለሀብቶችና መንግስታት ፍላጎታቸው የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብት መቀራመትና እራሳቸውን ማበልፀግ በመሆኑ አፍሪካ አዲስ የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ሰለባ ልትሆን ትችላለች ሲሉ ስጋታቸውን የገለፁትም በዚሁ ወቅት ነው፡፡

የአፍሪካ መሪዎች ከውጭ የሚመጡ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ እንዲገቡ ከመፍቀዳቸው በፊት ለህዝባቸው ዘላቂ የሆነ ልማትና ጥቅም ሊያመጣ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው ያሉት ሂላሪ ክሊንተን በተለይ ቻይና እንደ ግሪሳ ወፍ አፍሪካን መውረርዋን በእጅጉ ኮንነዋል፡፡

በቅኝ አገዛዝ ዘመን እንዳየነው ወደ አፍሪካ መምጣት በጣም ቀላል ነው፡፡የተፈጥሮ ሀብቶችን እየጫኑ ማግበስበስና መውሰድም እንደዚሁ ቀላል ነበር፡፡መሪዎች ጋር እየተመሳጠሩ የህዝቡን ሀብት እየጋጡ መሰወርም የተለመደ ነበር አሁንም ቻይና በቀላሉ አፍሪካ ውስጥ እየገባች መልካም አስተዳደርን ያላማከለ ስራ እየሰራች ያለች በመሆኑ ሁሉም የአፍሪካ መሪ ሊጠነቀቅ ይገባል ይሄን ደግሞ አሜሪካ በዝምታ አታልፈውም ሲሉ ማስጠንቀቂያ የሰጡት በዚሁ ዓመት ውስጥ ነው፡፡ ሂሊሪ ክሊንተን የሕዝብን መብት ለረገጠውና ሕዝብን ለሚጨፈጭፈው ለወያኔው አምገነን ቡድን በአመት ከ3 ቢሊዮን ዶላር አሜሪከ ስለምትሰጠው እርዳታ ግን ያነሱት ነገር የለም

እነ መለስ ዜናዊ 3 ወር ፕሮፓጋንዳ ሲሰሩበት የነበረውን የሄላሪ ጉብኝት ዛምቢያና ታንዛኒያ ከርመው እዚህም ይቆያሉ ተብሎ ሲጠበቅ 30 ደቂቃ ባልሞላ ውይይት ጥለዋቸው የሄዱትና የቡድኑን መሪዎች ያዋረዱትም በዚሁ ዓመት ነው፡፡

****

ዘንድሮ መለስ ዜናዊን እና ቡድኑን ያበሳጨው እና ያንገበገበው ጉዳይ ደግሞ ከኢትዮጵያ የተዛወሩት የዓለም ባንክ ከፍተኛ ባለስልጣን የአምስት ዓመቱን እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አስመልክተው በሰጡት አስተያየት ነበር፡፡

ባለስልጣንዋ ወያኔ እቅድ አወጣሁ ብሎ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ለፖለቲካ መጠቀሚያ ማዋሉን በመቃወም እቅዱም እንደማይሳካ በይፋ ከመቃወማቸውም በተጨማሪ የወያኔ ባለስልጣናት ያለ ፕሮግራም በግብታዊነት ከፍተኛ ገንዘብ የሚያፈሱትን የሀገር ሀብት መለስ ብለው ሊያጤኑት ይገባል ካሉ በሁዋላ ከዚህ ይልቅ የግል ኢንቨስትመንትን ማበረታታት......ህዝብ አሳታፊ የግብርና ፖሊሲ መንደፍ እና የትምህርት ጥራት ላይ አተኩሮ መስራት ተገቢ ነው ብለው ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች መግለጫ የሰጡትና የወያኔ ቡድን መሪዎችን የማደናገሪያ ፖለቲካ እርቃኑን ያጋለጡትም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ነበር፡፡

********

የወያኔ ቡድን በመሳሪያ ኃይል የሚፋለሙትን እና ለስልጣኔ ያሰጉኛል የሚላቸውን የሀገር ውስጥ ተቃዋሚ ቡድኖች እንዲሁም እውነተኛ ትችት የመሰዝሩበትን ምሁራኖች እያፈሰ ለማሰር እንዲመቸው ሽብርተኛ የሚል ህግ ያወጣውም በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነው።

እጅ አውጡ ሲባሉ የሚሰቅሉ .......አውርዱ ሲሉዋቸው የሚጥሉ የወያኔ አባሎች ብቻ በተሰባሰቡበት በዚሁ ምክር ቤት ተብዬ በተደረገ የምክር ቤት ስብሰባ ላይ በመሳሪያ የሚፋለሙትንና በሰላማዊ መንገድ የሚቃወሙትን የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎች እንዲሁም ነጻ አስተያየት እና ትችት የሚሰነዝሩበትን ዜጎች እያፈሰ ለማጎር እንዲመቸውና የአገዛዝ ዘመኑን በነጻነት ለማቆየት እንዲቻለው ማነቆ የሽብርተኛ ህግ በሚል አውጥቶዋል።

ከሀገሪቱ ለም መሬት እየተቆረሰ በኢንቨስትመንት ስም ለባዕዳኖች እና ለውጭ ባለሀብቶች መስጠቱን እንዲሁም በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እና ስቃይ በመቃወም ድምጻቸውን የሚያሰሙትንና የሚከራከሩትን ምሁራኖች፤ ጋዜጠኞችና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች አንደበት ለማዘጋት እና ለመድፈን ብሎም የስልጣኑን እድሜ ለማራዘም ሲል ብቻ የሽብርተኛ ህጉን አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሮዋል።

አስገራሚውና አነጋጋሪው የወያኔን አገዛዝ በመቃወም በመሳሪያ ኃይል የሚፋለሙትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሽብርተኛ ብሎ ሲፈርጅ ......ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይሎችን ያደራጃል.... ያሰለጥናል...... አልሻባብን በገንዘብ ይደግፋል...... እያለ ሲወነጅለው የነበረውንና የበረሀ አጋሩ የሆነውን ሻዕቢያ ሽብርተኛ ሳይል ማለፉ አነጋጋሪ ሆኖ ቆይተዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሽብርተኛ የሚለው ህግ በወጣ ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ይቃወሙኛል .....ይነቅፉኛል ብሎ በሚያስባቸው ዜጎች ላይ የጥቃት በትሩን የሰነዘረውም በዚሁ ወቅት ነው። አዋጁ ወጥቶ ፀደቀ በተባለ ጥቂት ቀናት ውስጥ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኛ የሆኑትን ከመኖሪያ ቤታቸው እና ከሚሰሩበት ቢሮ አፍኖ ለእስር ዳርጎዋቸዋል።

እርኩስ መንፈስ በላያቸው ላይ እንደ ጉልላት በተከመረባቸው ......ጥላቻ እንጂ ፍቅር በማያውቁ ......ቀን እና ሌሊት የማይለዩ...... የወያኔ የመረጃና የደህንነት ተወርዋሪ የፌዴራል ፖሊሶች ታፍኖ በእለተ ሰንበት የእረፍት ግዜውን ከባለቤቱና ከሕፃን ልጁ ጋር በመኖሪያ ቤቱ እያሳለፈ የነበረውን የአውራምባ ጋዜጣ አዘጋጅ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ታፍኖ የተወሰደው እና በማዕከላዊ ጭለማ እስር ቤት ውስጥ የተከተተው በዚሁ ህጉ በወጣ ሰሞን ነው።

የእሱን መታሰር ሰምተን ሰዓታት ሳንቆይ የፍትህ ጋዜጣ የአምድ አዘጋጅ የሆነችው መምህርት ርዕዮት አለሙም የዚሁ መጤ የወያኔ ቡድን የስልጣን ማራዘሚያ የሆነው የሽብተርተኛ ህግ ሰለባ የሆነችው በፀደቀ በጥቂት ቀናት ውስጥ ነው።

በዚህ ብቻ አላበቃም ወያኔ አወጣሁ ባለው ህገ መንግስት መሰረት በህጋዊ መንገድ በሀገር ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና በገጠር መንገድ ስራ ላይ የተሰማሩ መሀንዲሶችም የዚሁ ህግ ሰለባ ሆነዋል፡፡

በየሳምንቱ ቅዳሜ እየታተመ ሲሰራጭ የነበረው አዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች በሽብር ወንጀል ሊከሰሱ በዝግጅት ላይ እንደነበሩ ጥቆማ ስለደረሳቸው ሁሉም ከሀገር ጠፍተው ያመለጡትም መላው ኢትዮጵያ ህዝብ ግፍና መከራን እያስተናገደ ባሳለፈበት ዓመት ነው፡፡